# መግለጫ

የማይሆን ነገር የለምና የሚሆን ነገር ሁሉ ጊዜውን ጠብቆ ሲደርስ ታሪክ እራሱን ደገመ ይባላል:: ሰውም ታሪክን የሚማረው የሰው ልጆች ብዙ ጊዜ ከታሪክ የማይማሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ በመሆኑ፣ አንድ ሕብረ ተሰብ ያለ ተጠበቀ ሁኔታ ሻብ ሲልበት የ፤ እነ ዚህ መሆኑን ብናውቅ ኖሮ ይህ ነገር አይደርስም ነበር የሚሉ ዋ ራቸው በርከት ያለ ነው::

ጆርጅ ኦርዌል /GEORGE ORWELL / አኒማል ፋርም /ANIMAL FARM / የእንስሳት ገበርና የተባለች መጽሐፉን በ1945 ዓ.ም. ለዓለም ሲያበረክት የአምባገነን መንግሥት በሶቪዬት ዩኒየን የተከለውን የፖለቲካ አቋም ለመግለጽ እንጂ ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ሁኔታ ለማንፀባረቅ አልነበረም:: ትናንትም ሆነ ዛሬ፣ ቀይም ሆነ ጥቁር አምባገነን፣ የሕዝብን ነፃነት፣ መብትና እኩልነት ከዚህም አልፎ ሕልውናውን ጭምር የሚያከሽፍ አስተዳደር በመሆኑ በ 1945ዓ.ም. የታተመው የኦርዌል / ORWELL / ድርሰት የዛሬውን የኢትዮጵያን ችግር ቁልጭ አድርጎ ያቀርበዋል:: በብዙ ቦታ ላይ የጠቀሳቸው ነጥቦች ሲጠኑ ትንቢት ኢትዮጵያ መሰለው ይቀርባሉ::

በእንስሳት ምሳሌ የቀረበው የጆርጅ ኦርዌል ድርሰት ለባ ሞቀምና ስኖ ቦል / SNOWBALL AND NAPOLEON / በአንዱት ያለ ተ ገኮል የሕዝቡን የነፃነት ፍላጎት ለገል ጥቅማቸው እንዳዋሉት፣ ከ ዚህም በኋላ በሁለቱ መካከል የተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ያስከተለ ውን ጠንቅ ያሳያል:: ኦርዌል የአምባገነንነትን የፖለቲካ ሂደት በእንስሳት አስመስሎ ሲዘረዝር ለባ ሞቀም /NAPOLEON / በእንዱት ዓይነት ሁኔታ እራሱን ፈላጭና ቆራጭ ለማድረግ እንደቻለ በመግለጽ

ቶሎ ቶሎ ይህን በትክክል ከተናገረ በኋላ ግንባሩን ኮስኮስ አደረገና ወደ ግራና ወደ ቀኝ ከተመለከተ በኋላ አንስባቶን ከአግር እስከ ራሳቸው ገለምጦ በመካከላቸው "ጉራው ለመታረድ ተሸጠ" የሚባለው አስጸያፊ የሀሰት ወሬ እጅግ ያስቆጣው መሆኑንና የዚህ ዓይነት ወሬ የሚመነጨው ደደብ ከሆኑ አንስባት ብቻ መሆኑን ገለጸ። ከዚህም ቀጠል አድርጎ ጆሮቶን ቂኒር ቂኒር አያደረገ፣ የተወደደው ገናናው መሪያችን አባ ቀምቀም ይህን ያደርጋሉ ተብሉ መታሰቡ ራሱ አትዝብት ላይ የሚጥል ነው ቢል ምርር ባለ ቃል ገለጸና ሠረገላው ላይ የተጻፈው ጽሑፍ የከብት ጠኪጋሪውን ከመግዛቶ በፊት የነበረ መሆኑን አስረዳ።

አንስባቶ ይህን ከሰሙ በኋላ ትንሽ ልባቸው ተረጋጋ። ከዚህ በላይ አባ ቀምቀም ለጉራው ህክምና ከፍ ያለ ገንዘብ'ያወጡ መሆናቸው'ከተገለጸ በኋላ አንስባቶ የበለጠውን ተደሰቶ።

በማግስቶ በዋለው ስብሰባ ላይ አባ ቀምቀም ተገኘና፣ ስለ ጉራው አጠር ያለ መግለጫ ከሰጠ በኋላ የጉራውን አስከሬን ወደ አንስባቶ እርሻ ለማምጣት ባይቻልም ከሚቀበርበት ቦታ የሚቀመጥ አበባ ተዘጋጅቶ እንዲላክ አዘዘ። አባ ቀምቀም ንግግሩን ከጠረሰ በኋላ፣"አንስባቶ ሁልጊዜ ማስታወስ የሚገባችሁ ጉራው በሕይወቶ ባለ የሚጠቀምባቸውን 'እኔ ለአብዮቴ አቀደቃለሁ፣ አባ ቀምቀም አይሳሳቱም' በማለት የተጠቀመባቸውን መፈክሮች ነው፣ አለና አጀቡን አስከትሉ ተመለሰ።

ለግብዣ በተወሰነው ዕለት ከጉረቤት አገር ባንዱ ትልቅ



ሣጥን የታሸገ ዕቃ ወደአንስባቶ እርሻ ተጭኖ መጣ። በዚህ ዕለት ማታ ተሰምቶ የማይታወቅ ፈንጠዝያና ግርግር ከአሣሙራ መኖሪያ አካባቢ ያስተጋባ ጀመር። በማግስቶ ጧት የግርግሩን ሁኔታ በሹክሹክታ፣ አሣሙራን ከፍ ያለ ገንዘብ አግኝተው ምርጥ ዊስኪ ከወጭ አገር ያዘዙ መሆናቸው ይወራ ጀመር።

======

